Victorian Equal Opportunity
& Human Rights Commission

simply your rights

# በአግባቡ እና በእኩልነት ለመስተናገድ ያለዎ መብት

## Your Right to be treated Fairly and Equally

**ማንኛውም ሰው በአግባቡና እኩልነት በተሞላበት አቀራረብ ለመስተናገድ መብት አለው። በቪክቶሪያ ውስጥ በርስዎ ላይ አድልዎ፣ በወሲባዊ ጥቃትና የርስዎን ነገድ/ዘርና ሃይማኖት ስም በማጥፋት አስመልክቶ ችግር እንዳይፈጠርብዎት የሚከላከሉ ህጎች አሉ።**

### አድልዎ መፍጠር

አድልዎ መፍጠር ማለት አንድን ሰው በሚኖረው ይግሉ ባህሪ መቃረን ህገ-ወጥነት ነው። እነዚህም፡

- በእድሜ
- ጡት በማጥባት
- ተንከባካቢ በመሆን
- የአካል ጉዳት ወይም አካለጎደሎ በመሆን
- በጾታ ልዩነት
- በኢንዱስትሪ የሥራ እንቅስቃሴ
- ህጋዊ ባልሆነ ወሲባዊ አቀራረብ
- ባለትዳር በመሆን
- ወላጅ በመሆን
- በአካል ገጽታ
- በፖለቲካ ተሳትፎ ወይም እምነት
- ነብሰጡር በመሆን
- በዘር/በነገድ
- በሃይማኖት እምነት ወይም ተሳትፎ
- በጾታ
- በወሲባዊ አገላለጽ
- ከዚህ በላይ ካሉት ባህሪያት ካለው ሰው ጋር ግላዊ ግንኙነት መፍጠር ይሆናል።

### ወሲባዊ ጥቃት

በግብረስጋ ጥቃት ማድረስ ህገ-ወጥ ድርጊት ነው። ይህም ሳይፈለግ ወሲባዊ ንክኪት፣ ያልተፈለገ ወሲባዊ ጥያቄ ወይም ለወሲባዊ ግንኙነት የስድብ ጨወታ ወይም ቀልድ መናገርን ያካተተ ይሆናል።

### ፀረ-አድልዎና ወሲባዊ ጥቃት የት ቦታ ላይ ይፈጸማል?

ህጉ ተግባራዊ የሚሆነው በግል በሚፈጸም ላይ ሳይሆን በአደባባይ ህዝብ ፊት ለሚከሰት ባህሪያዊ ተግባር ነው። ይህም ማለት በሥራ፣ በመኝታ፣ ብክለቦች፣ በትምህርት፣ በእቃና አገልግሎት፣ በስፖርትና መሬት በሚሸጥበት ቦታ ላይ አድልዎ እና የወሲባዊ ጥቃት በህገ-ወጥ መንገድ ሲፈጸም ይሆናል።

### በዘርና ሃይማኖት ስም ማጥፋት

በዘርና ሃይማኖት ስም ማጥፋት ህገ-ወጥነት ነው። የዘርና ሃይማኖት ስም ማጥፋት ማለት በመሳደብ ወይም በአካል ጉዳት በማድረስ፣ በማስፈራራት እንዲሁም ለአንድ ሰው ወይም በቡድን ለተደራጁ በሚኖራቸው ዘር ወይም ሃይማኖት የጥላቻ መንፈስ ማሳየትና ለመጉዳት ከፍተኛ ጥረት ሲደረግ ነው።

### እኛን ስለተመለከተ

ሰዎች ስለአድልዎ፣ የወሲባዊ ጥቃት፣ በዘርና ሃይማኖት ስም ማጥፋት ለሚያቀርቡት ክስ/ቅሬታ በቪክቶሪያ የእኩልነት መብት አስከባሪ ኮሚሽን ለችግሮቹ መፍትሄ እንዲያገኙ ይረዳል። እነዚህ አገልግሎቶች በሚከተሉት መልኩ ይቀርባሉ፡

- ✓ በሚስጥራዊ
- ✓ በገለልተኛ ታዛቢ
- ✓ በነጻ
- ✓ በላሉ

የኮሚሽኑ ልዩ ፍርድ ቤት እንደ መደበኛ ፍ/ቤት አይደለም። ሰዎች በጋራ ስምምነት ለቀረቡት ክሶች መፍትሄ ያገኙ ዘንድ እንረዳለን። ሰውን አንወነጅልም፣ በሌላ ላይ ፍርድ አንሰጥም ወይም ለተበደለ መካካሻ አንሰጥም።

### ክስ ስለማቅረብ

በወሲባዊ ጥቃት ወይም በስም ማትፋት ልዩነት በመፍጠር በደል ደርሶብኛል ብለው የሚያምኑ ከሆነ ለኮምሽኑ ክስ/ቅሬታ ማቅረብ ይችላሉ።

አስተርጓሚ ካስፈለግዎ ለኮሚሽኑ በመደወል በነጻ እንዲቀርብልዎ መጠየቅ ነው። ክሱን በማቀነባበር ላይ የሥራ ባልደረባችን ይረዳዎታል እንዲሁም ክሱ የተመሰረተበትን ሰው ያነጋግራል። እኛ ለአንደኛው ወገን አናዳላም እንዲሁም የቀረበውን ክስ ሚስጢራዊ በሆነ መንገድ ይጠበቃል።

አንድ ሰው ያለአግባብ ካስተናገድዎት ወይም ለኮሚሽኑ ቅሬታዎን በማቅረብዎ ካስፈራራዎት ህገ-ወጥ ነው።

### ለክሶች መፍትሄ ስለማግኘት

ለክሶች መፍትሄ ለማግኘት ብዙ መንገዶች አሉ። የሥራ ባልደረባችን ያሉትን አማራጭ መንገዶች በመግለጽ ወደ መፍትሄው ደረጃ ለመድረስ ያስችላል።

ለኮሚሽኑ ክስዎን ለማቅረብ የህግ ጠበቃ ላያስፈልግዎ ይችላል፣ ነገር ግን አንዳንድ ሰዎች የህግ ጠበቃ፣ አማካሪ ወይም የሚረዳቸው ሰው አብሮ ሲኖር በበለጠ ምቾት ይሰማቸዋል።

**ለምክር መስመር (03) 9281 7100**
**በነጻ ለመደወል (በገጠር ሆኖ ለሚደውል)**
**1800 134 142**
**መስማትና መናገር ለማይችል/TTY:**
**(03) 9281 7110**
**ኢሜል: complaints@veohrc.vic.gov.au**

በጥያቄ ነጻ የአስተርጓሚ አገልግሎት ይቀርባል።

**የክህደት ቃል**: ይህ ለመረጃ አቅርቦት መመሪያ ብቻ ተብሎ የቀረበ ነው። የህጋዊ የሆነን ምክር አይተካም።
**የርስዎ ብቻነት**: በቪክቶሪያ ነዋሪዎች የብቻነት ህጎች ላይ በእኩልነት መብት አስከባሪ የ1995 ዓ.ም አንቀጽ ህግ መሰረት የVEO&HRC ይከተላል። የብቻነት ፖሊሲያችን በድረገጽ፤ www.humanrightscommission.vic.gov.au/privacy ላይ ይቀርቧል ወይም ኮሚሽኑን ማነጋገር ይሆናል።
በቪክቶሪያ እኩልነት መብት አስጠባቂና በሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን አድራሻ፡ 3/380 Lonsdale St, Melbourne, Victoria, 3000 ፈቃድ የወጣ የታትመ ጽሁፍ ነው።

April 2007